# ስለድርድር ሂደት

ድርድር/ሽምግልና ወላጆች ለገልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደት ያላቸውን መብት አይነፍግም አያጓትትምም፡፡

❧

ድርድር ገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ወ ም ለገለተኛ የቅሬታ አፈታት ጥያቄው በቀረበበት ተመሳሳይ ወቅት ሊጠየቅ ይችላል፡፡

❧

በድርድር/በማደራደር ሙያ የሰለጠነ የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ የድርድሩን ሂደት ይመራል፡፡

❧

በድርድር ችሎቱ ጠበቆችና የህግ ድጋፍ ሰጪዎች/ደጋፊዎች ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

❧

በድርድሩ አማካኝነት የተደረሱ ስምምነቶች በጽሁፍ ከተቀመጡ በኋላ በሁሉም ወገኖች ይፈረማሉ፡፡

❧

በድርድሩ ወቅት የተያዙ ማንኛቸውም ኢንፎርሜሽን በምስጢር ተጠብቀው ይያዛሉ፡፡

---

ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን ይፈልጋሉ? እንግዳውስ ቀጥሎ የተመለከቱት ማጣቀሻዎች ስለቅድመ-ጣልቃገብነት ዘዴ የወላጆች መብቶች የበለጠ ኢንፎርሜሽን ይሰጡዎታል፡፡

- አካባቢያዊ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ በማለት ላይ ያሉ ልጆች ፕሮግራም አስተባባሪ፡፡
- አካባቢያዊ የህግ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች፤ ለምሳሌ፡

  *Advocates for Children and Youth, (410) 547-9200*

  *Family Support Network for Infants and Toddlers With Special Needs, (410) 767-0652, (800) 535-0182*

  *Maryland Disability Law Center, (410) 235-4700, (800) 233-7201; TTY: (410) 235-4227*

  *University of Maryland School of Law General Practice Clinic, (410) 328-3295*
- የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል
  የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት፤
  **Maryland Infants and Toddlers Program**
  200 West Baltimore Street; Baltimore, MD 21201
  (410) 767-0261 በድምጽ • (800) 535-0182 የድምጽ ነጻ ጥሪ
  (410) 333-8165 ፋክስ • (410) 333-0731 TDD

---

Robert L. Ehrlich, Jr.
ገዢ

Edward L. Root
*ፕሬሲደንት፤ የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ቦርድ*

Nancy S. Grasmick
*የክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ*

Carol Ann Baglin
*ረዳት የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ*
*የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት*

የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል፤ ለቅጥር ሥራም ሆነ ፕሮግራምን ለመጠቀም፤ በዘር፤ በቀለም፤ በጾታ፤ በእድሜ፤ በትውልድ ወይም ብሄር፤ በሃይማኖት፤ ወይም በአካል-ጎደሎነት ላይ የተመሰረተ ልዩነት አያደግም፡፡ የዲፓርትሜንቱን ፖሊሲ በተመለከተ ጠይቆ ለመረዳት፤ የዕኩልነት ዋስትና አስከባሪ ቅርንጫፍን በሚከተሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ፡፡ Equity Assurance and Compliance Branch 410-767-0246 በድምጽ 410-333-2226 ፋክስ ወይም 410-333-6442 TDD. ✦ ይህ ሰነድ ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ክፍል፤ የልዩ ትምህርት ክፍልና የማህበራዊ ባህሪያት ማረሚያ ቢሮ፤ IDEA፤ ክፍል C፤ እርዳታ #H181A020124. ✦ በተገኘ ገንዘብ፤ በልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ቅርንጫፍ አማካኝነት ተቀነባብሮ የታተመ ነው፡፡ ✦ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች የግድ የዩናይትድ ስቴትስን የትምህርት ክፍል ወይም የማንኛውንም ሌላ የፌደራል ኤጀንሲን አመለካከት የሚያንጸባርቁ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ስለሆነም በዚህ መልኩ መታየት የለባቸውም፡፡ ኢንፎርሜሽኑ ከህትመት ባለቤትነት የመብት ገደብ (ኮፒ ራይት) ነጻ ነው፡፡ አንባቢዎች ቅጂውን እያባዙ እንዲያዳርሱና እንዲያስነብቡት ይበረታታሉ፤ ነገርግን፤ እባከዎ ይህ ሰነድ፤ በሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ቅርንጫፍ የስራ ውጤት ለመሆኑ ተገቢውን ዋጋ ይስጡ፡፡ ✦ የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን ድንጋጌ (ADA)ን በሚመልከት ሲጠየቅ፤ ይህ ሰነድ በሌላ የተለየ አማራጭ አቀራረብ ተዘጋጅቶ ይገኛል፡፡ የልዩ ትምህርት ክፍሉን በሚቀጥሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ፤ 410-767-0261 በድምጽ፤ 410-333-2661 ፋክስ፤ 410-333-0731 TDD.

3/04

---



# ድርድር በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት

የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት፤
የሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ የሚሉ ልጆች ፕሮግራም

Amharic

አንዳንድ ጊዜ፣ ስለ አንዳንዶቹ የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት አካሄዶች ላይ የአገልግሎቱ አቅራቢዎችና ወላጆች የማይስማሙባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህም ቀጥሎ ያሉትን ይጨምራሉ፣

- ባለመብትነትን ስለመወሰን
- አንድን ሕጻን ስለማመዛዘንና መገምገም
- መብቱ ላለው ለጋ ሕጻን ወይም ድክ-ድክ የሚል ልጅ አገልግሎቶችን ስለማቅረብ
- ለፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት የወላጆች ገንዘባዊ ግዴታ

ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ መግባብት በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፣ እናም ሁለቱ ወገኖችም በጋራ የሚያስማማቸው ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይሳናቸዋል።

ቅሬታዎቻቸውን/ችግሮቻቸውን ለማስተናገድ ለወላጆች ያለው አንዱ አማራጭ ገለልተኛ የችግር አፈታት ሂደት—ጉዳዩ በሚሰማበት ወቅት በሚቀርቡ ማስረጃዎች ላይ በመመስረት፣ በአስተዳደራዊ ህግ ዳኞች አማካኝነት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚከናዎንበት ሥርዓታዊ ሂደት ነው። ይህን አማራጭ ለሚመለከት ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን፣ *ገለልትኛ የቅሬታ አፈታቶች ሂደት* በሚል ርዕስ የሚታወቀውንና ከሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ የሚሉ ልጆች ፕሮግራም ማግኘት የሚቻለውን የጽሁፍ መግለጫ ይመልከቱ።

**ድርድር** ወላጆች ችግሮቻቸውን ለማቃለል የሚጠቀሙበት መለስተኛ ህገ-ሥርዓታዊ አማራጭ ነው። እሱም፣ በወላጆችና በአገልግሎት አቅራቢዎች መካከል ያለውን ያጋራ አሰራርና የጋራ የስራ ግንኙነትን ለማጠናከር በሚረዳ መልኩ የጋራ ችግሮችን ለመፍታ ግልጽ በሆነ ንግግርና መግባባት ላይ ያተኩራል። ድርድር ፍጹም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው—ወላጆች በገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደት ምትክ፣ ወይም በተጨማሪ የድርድር ችሎትን የመጠየቅ መብት አላቸው።

---

በገለልተኛ አደራዳሪነት በሰለጠነ አደራዳሪ ምክርና እገዛ ሥር በሚደረግ ድርድር፣ በአንድ አከራካሪ ጉዳይ ላይ ያሉ ወገኖች ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ ያስችላቸዋል። አድራዳሪውም ውይይቱ በቤተሰብና በአገልግሎት አቀራቢው ድርጅት መካከል ያለው የልዩነት ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል። ሁለቱም ወገኖች የመረጃ ጭብጦችንና ሃሳቦችን የማቅረብ መብት አላቸው፣ ከዚያም አደራዳሪው የሕጻኑንና የቤተሰቡን ጥቅምና ፍላጎት በሚያስከብር መልኩ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ያመቻቻል።

አንድ ሕጻን ተገቢውን የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች በአግባቡ እያገኘ መሆኑን ማረጋገጥ የአደራዳሪው ዋነኛ ግብ ሲሆን፣ ወላጆችና የአገልግሎቱ አቅራቢዎችም ይህ ሁኔታ በመልካም መንፈስ በስራ ላይ ይውል ዘንድ ከሚያስችል ውሳኔ ላይ ለመድረስ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል።

በድርድሩ ምክንያት ከስምምነት ላይ ከተደረሰ፣ ያ ስምምነት በጽሁፍ ይቀመጥና ሁሉም ወገኖች ይፈርሙበታል።

ከስምምነት ላይ ካልተደረሰ፣ ወላጆች አሁንም ገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደትን የመጠየቅ መብት አላቸው።

በማንኛውም ሁኔታ፣ አደራዳሪውና ሁሉም ወገኖች የድርድሩን ሂደት ምስጢራዊነት መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

## ድርድርን ለመጠየቅ፣ ወገኖች ምናልባትም፣

- *ለፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ድርድር፣ ማመልከቻዎን ለሜሪላንድ የአስተዳደራዊ ችሎት ቢሮ ያቅርቡ። ወላጆችና አገልግሎት አቅራቢዎች በጋራ የሚያስማሟቸው ውሳኔዎች ላይ እንዲደርሱ ለመርዳት የሰለጠኑ አደራዳሪዎች ይገኛሉ።*

*ወይም*

- ከገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደት አስቀድሞ ድርድር እንዲደርግ የሚሹ ሲሆኑ፣ ይሄንኑ የጽሁፍ አቤቱታዎን ለሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ የሚሉ ልጆች ፕሮግራም ይላኩ።

የሕጻኑ ደህንነት ቁልፉ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን፣ በወላጆች በሚቀርቡ ቅሬታዎች/አቤቱታዎች ምክንያት የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች አይይስተጓጎሉም ወይም አይቋረጡም።